

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በትግራይ ክልል በመቐለ ሃገረ ስብከት የማኅደረ ሰብሐት ቅድስተ ቅዱሳን ማርያም ካቴድራልና ቅዱስ ሩፋኤል ሰ/ት/ቤት



ወይ አዳም

ትዕይንት ፩

- ከመድረኩ ላይ አንድ ሰው የኔቢጤ ልብስ ለብሶ ምሳር ይዞ እንጨት ሲፈልጥ ይታያል። ሰውየው ለደረሰበት ችግር እና መከራ ሁሉ አዳምን ሲወቅሰው ይደመጣል።

ሰውየው፡- ወይ አዳም/ይ/ አንተ ባትበድል አንተ ባታጠፋ ያኔ ዕፀ በለሷን ባትበላ ኑሮ እኔ ድሃ ባልሆንኩኝ ነበር። ወይ አዳም አንተ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ባታፈርስ ባትጥስ ኑሮ እኔ ዛፍ ቆራጭ እንጨት ፈላጭ ባልሆንኩ። የአንተ ጦስ ይኸው እኔ ድሃ አደረገኝ፣ ወይ አዳም አንተ ባትበድል፣ አንተ ባታጠፋ፣ አንተ ሕገ እግዚአብሔር ትእዛዘ እግዚአብሔር ብታከብር ኑሮ ሀብቴ ተትረፍርፎ፣ ዝናዬ ገዝፎ፣ በደስታ እና በሐሤት እኖር ነበር። ወይ አዳም .... ወይ አዳም ..... ወይ አዳም .....

- ከመድረኩ ፊት ለፊት አንድ ጥቁር ካፖርት የደረቡ ባለጠጋ .... ሰወየው የተናገረውን ካዳመጡ በኋላ ጠጋ በማለት እንዲህ ይሉታል

ባለጠጋ፡- ለመሆኑ ይህን ቅዱስ የእግዚአብሔር ሰው አዳምን ምን ቢበድልህ ነው እንዲህ የምትለው?

ሰውየው፡- (ደንገጥ ብሎ) እንዴ ጌታዬ እርሱ ባጠፋው ጥፋት አይደለም እንዴ እኔ ድሃ የሆንኩት

ባለጠጋ፡- እንዴት ወዳጄ?

ሰውየው፡- እንዴት ማለት ጥሩ! አዳም ዕፀ በለስ ቀጥፎ ባይበላ የጌታን ሕግ ቢጠብቅ እኔ በስንት ስቃይ የምበላውን እንጀራ፣ የምጠጣውን ውሃ በቀላሉ አገኝ ነበር። አሁን ግን የእርሱ በደል ለኔ ተረፈ .... ወይ አዳም

ባለጠጋ፡- በል እንግዲህ አዳምን መውቀስ ተወውና ከዛሬ ጀምሮ እንጨት ከምትፈልጥበት ሥራ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ተላቀህ እኔ በምሰጥህ ሀብት እና ንብረት ትዳር መሥርተህ በደስታ ትኖራለህ።

ሰውየው፡- አቤት የእግዚአብሔር ሥራ! ተመስገን.... ተመስገን .... አመሰግናለሁ ጌታዬ(እግራቸው ስር ይወድቃል)

ባለጠጋ፡- ተነሥ ተነሥ.... ተነሥ ተከተለኝ ወዳልኩህ ቦታ ልውሰድህና

ሰውየው፡- እሺ ጌታዬ (ተያይዘው ይወጣሉ)

ትዕይንት ፪

ሚስት፡- አሁን ይህንን ቤት ለተመለከተ ሰው ሁሉ የዚህ ቤት እመቤት ትጎርሰው ትጠጣው ዘንድ ምንም ያልነበራት ሚስኪን ድሃ ነበረች ቢባል ማን ያምናል? ይህንን መስክ፣ ይህንን ቦታ፣ ይህንን ሀብት በሙሉ ላስተዋለ ሁሉ የሆነ ጊዜ ላይ አንድ ወቅት ላይ ወይ ሔዋን ወይ ሔዋን አንቺ የችግሬ ምንጭ አንቺ ነሽ እያለች ሔዋንን ትሳደብ የነበረችው የአንድ ሴት ንብረት ነው ቢባል እንዴት አድርጎ ማመን ይቻለዋል፣ ነገር ግን ሁሉም አልፏል..... ተመስገን ነው የሚባለው።

ሰውየው፡- (ከበስተጓላዋ ላይ ቁሞ እያዳመጣት ይቆይእና) እውነትሽ ነው ተመስገን ነው የሚባለው። ዐየሽ የኔ እመቤት! ጌታዬ ታላቅ ነገር አድርገውልኛል፣ ከድህነት ቀንበር አላቀው ለዚህ ክብር አበቁኝ፣ አንችን የመሠለች ሚስትንም ሰጡኝ። ዋጋቸው የሰማይ አምላክ ይክፈላቸው

ሚስት፡- ትክክል ነህ የኔ ጌታ! ላንተም ይሁን ለኔ ጥሩ ውለታ አድርገውልናል፣ ከምናስበውም በላይ መልካም ናቸው።

ሰውየው፡- አሁን ጌታችን ላደረጉልን ውለታ መመስገን ብቻ ሳይሆን አድርጉ ያሉንን ሁሉ በታማኝነት መፈጸም አለብን።
ሚስት፡- ለዚህ ክብር የበቃን በማን ሆነና?
ባለጠጋ፡- (የሆነ እቃ በካርቶን/ወይም በሌላ ነገር/ ይዘው ይገባሉ) ሰላም ለዚህ ቤት እንደምን አለችሁ?
ሰውየው እና ሚስቱ፡- እግዚአብሔር ይመስገን ደኅና ነን። እንደምንዎት ጌታዬ? ይቀመጡ....
ባለጠጋ፡- ደኅና ነኝ እግዚአብሔር ይመስገን! አመሰግናለሁ ስለምቸኩል ልሂድ.....ባይሆን አንድ አደራ ላስቀምጥ ፈልጌ ነበር።
ሚስት፡- እሺ ጌታዬ ... ግን አደራው ምንድን ነው?
ባለጠጋ፡- እኔ ወደ የውጭ ሀገር ሰለምወጣ ይህንን እቃ እስክመለስ ድረስ እናንተ ዘንድ በአደራነት ይቆይ። እባካችሁን ይህንን የከበረ የአደራ እቃ እስክመጣ ድረስ ሳታበላሹ በጥሩ ቦታ አስቀምጡልኝ። አደራ... (እቃውን ሰጥተው ይወጣሉ)
ሰውየው፡- እሺ ጌታዬ አደራችንን በእምነት እንዋጣለን .... ማሬ በጥሩ ቦታ አስቀምጭው
ሚስት፡- እሺ ማሬ (እቃውን ይዛ ትወጣለች)
ባለጠጋ፡- ደህና ሰንብቱ(ተሰናብቶ ይወጣል)
ሰውየው፡- (ደጅ ደጅ እያየ) ወይ ግሩም የዛሬን አያድርገውና ያኔ ድሃ በመሆኔ ብቻ ማንም አያምነኝም ነበር? ዛሬ ግን ዕድሜ ለጌታዬ ይሁንና ለዚህ ክብር በቃሁ። ውዴ አስቀመጥሽው
ሚስት፡- አዎ የኔ ጌታ...ግን እኔ የምልህ ስጦታው ምንድን ነው? አይታይም እንዴ?
ሰውየው፡- ደሞ ምን አመጣሽ? አደራ ብለው... እንዳንከፍተው አስጠንቅቀውን... ከሄዱ በኋላ ምንድን ነው? ትያለሽ እንዴ? የፈለገውን ይሁን።
ሚስት፡- ውዴ አንድ ነገር ልጠይቅህ?.... ስጦታውን ብናየው ምን አለበት?
ሰውየው፡- ምን? ምን እያልሽ ነው? የአደራ እቃ መሆኑን ዘነጋሽው እንዴ? የተሰጠነው እንድንጠብቀው እንጂ እንድናበላሸው አይደለም፤ ይልቅ አደራችንን እንጠብቅ።
ሚስት፡- ትንሽ ነው ከፈት የምናረገው... ደግሞም አስቀምጡት አታበላሹት እንጂ አትክፈቱት አልተበላልንም። ካየነው በኋላ እናሸገዋለን።
ሰውየው፡- አይሆንም! አስቢው ይህንን በመሠለ ቤት ያኖሩን አክብረው የሾሙን ሰው እንዴት አደራ በመብላት እናዛዝናለን።
ሚስት፡- አንተ ደግሞ አስቢ ትለኛለህ እንዴ? አስቤ እኮነው ይህን የምልህ ። ይህንን ሁሉ ሃብት ንብረት ሲሰጡን አንዳችም ቃል አንዳችም አደራ አልሰጡንም ታዲያ ዛሬ እንደዚህ ያሉን ከሰጡን ነገር ሁሉ ቢልቅ አይደለምን?
ሰውየው፡- አይሆንም!.... አይከፈትም!.....
ሚስት፡- በል እስከዛሬ መልካም ባል ነበርክ ከዛሬ ጀምሮ ግን በአንድነት አንዘልቅም ደህና ሁን! መሄዴ ነው።
ሰውየው፡- ቆይ ቆይ ምን እያረግሽ ነው?
ሚስት፡- ስማ በዚህ ትንሽ ነገር መስማማት ካቃተን እንዴት ብለን ነው በጋራ የምንኖረው?
ሰውየው፡- ካንቺ በልጦብኝ ሳይሆን ነገሩ አደራ ሰለሆነ ነው።
ሚስት፡- አደራን አናክብር አላልኩህም እኔ እያልኩ ያለሁት እንክፈተው አይተን እንዘጋዋለን ነው።
ሰውየው፡- ግን እኮ የአደራ እቃ....
ሚስት፡- እንግዲህ ደሜን አታፍላው መሄዴ ነው።

ሰውየው፡- እሺ እንክፈተው
ሚስት፡- ጎሽ የኔ ጌታ የኔ ባትሆን ይቆጨኝ ነበር። (ካርቶኑን በመክፋት ላይ እያሉ እቃው ቀድቆ ይሰበራል)
ሚስት፡- አንተ ለምን ሰበርከው?
ሰውየው፡- ለምን ሰበርከው? ራስሽ ነሽ የሰበርሽው።
ሚስት፡- ባንተ በኩል ሽልኮ አይደለም እንዴ የወደቀው።
ሰውየው፡- ቢሾልክስ? እኔ ነኝ የሰበርኩት?
ሚስት፡- ታድያ ማን ሆነና?
ሰውየው፡- አንቺ
ሚስት፡- አንተ ነህ የሰበርከው
ሰውየው፡- አንቺ ነሽ (አንተ ነህ፥ አንቺ ነሽ እያሉ ሰጨቃጨቁ ባለጠጋው ይገባሉ)
ባለጠጋ፡- ጤና ይስጥልኝ እንደምን ናችሁ? ደህናም አይደላችሁም እንዴ?
ሰውየው እና ሚስቲ፡- አብሮ ይስልን፤ ደህና ነን። ምነው ምን ሁነው ተመለሱ?
ባለጠጋ፡- አንዳንድ ነገሮች ስላልተመቻቹ ከሀገር ቤት የምወጣው በሚቀጥለው ሳምንት ነው። ሰለዚህ የአደራ እቃዬን ስጡኝ እና ፈጠን ብዬ ወደ ሥራዬ ልሂድ።
ሰውየው እና ሚስቲ፡- የምን የአደራ እቃ?
ባለጠጋ፡- ዛሬ ጥዋት መጥቼ ያስረከብኳችሁ ነዋ።
ሰውየው፡- ውይ ዘነጋነው.... እእእ...ቃውን አምፅው
ባለጠጋ፡- አስቸገርኩ አይደለም ... መቸስ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ነው የሚባለው። (እቃውን ተቀብለው) ምነው ቀለለኝሳ?
ሰውየው እና ሚስቲ፡- (እሱ ነው፥ እሷ ነኝ እያሉ ይጨቃጨቃሉ)
ባለጠጋ፡- ድሮ አንተ አባቻትን አዳምን አንቺ ደግሞ እናታችን ሔዋንን ለምን ሕገ እግዚአብሔርን ጣሱ ስትሉ እነርሱን ትሰድቡ ታቃልሉ ነበር፤ ነገር ግን እናንተም የተሰጣችሁን አደራ እልተዋጣችሁም፤ ስለዚህ ለእናንተ ክብር አያስፈልግም (የሰጣቸውን ልብስ ያወልቅላቸዋል) ዉጡ ዉጡ ነው የምለው(ከቤቱያባርራቸዋል)። (እያለቀሱ እያዘኑ ይወጣሉ... እያለቀሱም ሳለ ሰውየው ሚስቱን ያባርራታል... ለየብቻም ሁነው መልቀስ ይቀጥላሉ.... ከመድረክ ጀርባ መዝሙር ይዘመራል)
ከመድረክ፡- በዕለተ ዓርብ ሥላሴ ሰውን ፈጠሩ እንደ መልካቸው
የተፈጠሩትም አዳም ሔዋን ናቸው
በጠቅላላው ዓለም ኃይልን ሲሰጣቸው
አጥፍተው ወደቁ በሰይጣን ተሳስተው . . . . . ወይ በደል ወይ ጉዳት
የሁላችን አባት አዳም ያንጊዜ ጀመረ ልቅሶውን
ተሳስቶ በመብላት ዕፀ በለሱን
ሊወርስ ፈልጎ አምላክነትን
ላይሆነው መካሪ ያክፉ ሰይጣን . . . . . ወይ በደል ወይ ጉዳት
ሰውየው፡- ከጎኔ ተፈጥረሽ ሔዋን እንኳን ልትረጂኝ ጎዳሽኝ
አንችም ተሳስተሽ እኔን አሳትሽኝ
በማሥመሰል ነግሮሽ ስላስበላሽኝ
እስከ መቼምው ድረስ ሙቼ ቀረሁኝ . . . . . ወይ በደል ወይ ጥፋት
ሚስቲ፡- አትውቀሰኝ እንጂ አዳም ምንላድርግ ብለህ ነው ጌታዬ ...
ሰይጣን አስቶኝ ነው አወይ መከረዬ
እስከ መቼው ድረስ ልዘልቀው ኑሮዬ
ስለ ተጣላሁኝ ከቸሩ ፈጣሪ . . . . . ወይ በደል ወይ ጥፋት

<u>ሰውየው</u>፦ ያችን ዕፀ በለስ ባትቆርጫት ከሰይጣን ጋር ተማክረሽ
የምድሩን ሳይበቃሽ የሰማይን ሽተሽ
እኔን አዋረድሺኝ አንቺ ተዋርደሽ
ከእንግዲህ ቀረ ከንቱ ምኞትሽ . . . . . ወይ በደል ወይ ጥፋት

<u>ከመድረክ</u>፦ ያንጊዜ ከገነት ሲወጡ በጥፋት ሲገፈፍ ክብራቸው
መጣላት ጀመሩ እርስ በራሳቸው
<u>አንቺ ነሽ አንተው ነህ ሆነ ነገራቸው</u>
<u>ከንግዲህ ላይጠቅም መነዛነዛቸው</u> /፪/
ወይ በደል ወይ ጉዳት

ወስብሐት ለእግዚአብሔር
ወለወላዲቱ ድንግል
ወለመስቀሉ ክቡር